# “የአንድነት ዜማ     እንተባበር"ሁሉም ዘብ ይቁም በቦታው”

“ለአማራ ህዝብ “የቀረበ ጥሪ !!!

29 september 2016

አማራነትን መስበክ ሀጢያት ወይም ወንጀል አይደለም፣ አማራነትን መስበክ በወያኔ የጎጥ ፖለቲካ ቋት ውስጥ ገብቶ ዘረኝነትን ማቀንቀንም አይደለም፣ ከሁሉም በላይ አማራነት ነፃነትና ኢትዮጵያዊነት የነፃነት እምነት ነው። ። አማራ ኩሩና አትንኩኝ ባይ ህዝብ ነው፣ አማራ አኩሪ በህልና ወግ ያለው፣ይሉኝታና ውለታን የሚያውቅ፣እንግዳ ተቀባይ ፣ሰው አክባሪ ፣ካልነኩት የማይነካ ፣በሀገሩና በድንበሩ ቀልድና ይቅረታ የማያውቅ፣ በፍቅር እንጂ በጥላቻ ሽንፈትን የማይቀበል፣ የራሱን የማይሰጥ የሰው የማይመኝ፣ የማይነካ ለሀገሩና ለሀይማኖቱ ቀናኢ የሆነና ፈሪሃ እግዚአብሄር ያለው ህዝብ ነው። አማራ ማስመሰል የማያውቅ ፍቅርና ጠላቻውን ፊትለፊት የመግለፅ ድፍረት ያለው ህዝብ ነው።፣ለጠላቱ ኮሶ ለወዳጁ፣ቅን የሆነ ቅን ህዝብ ነው። አማራ የለም ሲባል የሚኖር አለቀ ሲሉት የሚበዛ፣ ጥላቻን በፍቅር የሚገዛ፣ ለወዳጆቹ ጋሻና መከታ፣ ለጠላቶቹ ፍም እሳት ረመጥ፣ የጋለ የብረት አሎሎ የሆነ ለጠላቱ የማይጨበጥ ህዝብ ነው።

አማራ በአማራነቱ ይሰባሰብ፣ ይደራጅ ፣ይታጠቅ ስንል በአማራነቱ ብቻ ተለይቶ እንደ እብድ ውሻ ተደብድቦ ከሚደርስበት የጅምላ ጭፍጨፋና የዘር ፍጅት እራሱ መከላከል እንዲችል ለማስቻል እንጂ ፣የአማራን ኢትዮጵያዊነት ጥያቄ ላይ ጥሎ የወያኔን የጎሳ ፓለቲካ ለማቀንቀን አይደለም። አበው " እሾህን በእሾህ " እንደሚሉት ወያኔን በቆፈረው ጉርጓድ ውስጥ ለመቅበር በመረጠው የትግል ስልት መጋፈጥ የግድ ይላል። ወያኔ ለዚህ እኩይ ተግባሩ" አማራ ቀንዳምና ጅራታም ተናካሽ አውሬ ነው፣ አማራ ከምድረገፅ መጥፋት ያለበት ታሪካዊ ጠላታችሁ ነው " እያለ ቀስቅሶ በፀረ አማራ   ትግሬውን   ከጎኑ እንዲሰለፍ ያደረገው በኢትዮጵያዊነት ስሜት ሳይሆን በትግሬነቱ   በዘረኝነት መንፈስ በመቀስቀስ ነው።

አማራ በአማራነቱ ብቻ በእሳት ተቃጥሏል።በጥይት ተገድሏል፣ ከገደል ተጥሏል፣   የዘር ፍጅት ደርሶበታል፣ተፈናቅሏል ተሰዷል፣ታስሯል፣ ተዋልዶ ዘሩን እንዳይተካ መካን ተደርጓል፣ ተዋረዷል ተንቋል፣ ይሄ ሁሉ ሲሆን አይዞህ አለንልህ ብሎ ሊታደገው የሞከረ ማንም የለም። ሁሉም በየጎጡ ተደራጅቶ የጋራ ጠላቱን በጋራ ሲከላከል፣ አማራ ግን በኢትዮጵታዊነት ፀንቶ በጎሳ ከረጢት ውስጥ ሳይገባ እስካሁን የሚደርስበትን ግፍና ሰቆቃ ችሎ ቆይቷል ፣ አሁን ግን የግፉ ዋንጫ ሞልቶ ስለፈሰሰ አምርሮ እምቢ! ብሎ ተነስቷል።አማራ በተለያዩ ክልሎች በግፍ የተጨፈጨፈው አማራ መሆን ወንጀል ነው !   ጎጃሜ፣ወሎዬ ፣ሸዌ ጎንደሬ እየተባለ ሳይሆን አማራ ተብሎ ብቻ ስለሆነ የተጀመረው ፀረ ወያኔ እራስንንና ሀገርን የመከላከል ትግል በድል ወደፊት መራመድ ካለበት በየትኛውም የሀገሪቱ ክልል የሚኖር አማራ በአንድላይ መቆም አለበት፣ ሁለትና ሶስት አይነት አማራ የለም የትም ይኑርየትም አማራ ሁሉ አንድ ነው፣”አማራ “!!! አንድነት ሀይል ነው፣ ማንም ወደደ ጠላ በአማራነቱ ይሰባሰባል፣ይደራጃል፣ ይታጠቃል ፣ ሊየጠፉት የተነሱበትን ጠላቶቹን እንደ አማራ ተደራጅቶ ፊትለፊት ይጋፈጣቸዋል።

ስለዚህ በዚህ ትግል " በመረጠው ዳኛ የሚረታና በቆረጠው ዱላ የሚመታ" ማን ሊሆን እንደሚችል እየቆየን እናያለን። እስካሁን ባለው ሁኔታ በመላው የሀገሪቱ ክልሎችአማራውን ጨርሶ ለማጥፋት

እየተደረገ ያለው የዘር ፍጅት አማራ በመሆኑ ብቻ እንጂ ወሎዬ ፣ጎጃሜ፣ ጎንደሬ ሸዌ በመሆኑ አይደለም። ስለዚህ የትም ይወለድ የትም ይኑር አማራ አማራ ስለሆነ ጎንደሬ ፣ጎጃሜ፣ ወሎዬ፣ሸዌ እየተባለ በጎጥና በመንደር የሚደረገው መሰባሰብ የተባበረውን የአማራ ህዝብ ትግል የሚያኮሰምን ከመሆኑም በላይ ለተናጠል ጥቃት የሚያጋልጥ ነው። የዚህ አይነቱ የአማራ ልጆች መከፋፈል ደግሞ የሚጠቅመው ወያኔን ብቻ ነው። ይህ የገባንበት የአልሞት ባይ ተጋዳይነት ትግል ወያኔን ለመከላከልና መልሶም ለማጥቃት የመረጥነው ታክቲክና አስትራቴጂ ወደንና ፈልገን የገባንበት የትግል ስልት " እሾክን ነእሾክ" በሚባለው አማራዊ ስልት ነው።ስለሆነም የተጀመረው ፀረ ወያኔ እራስንንና ሀገርን የመከላከል ትግል በድል ወደፊት መራመድ ካለበት በየትኛውም የሀገሪቱ ክልል የሚኖር አማራ በአንድላይ መቆም አለበት፣ወያኔ ያለርህራሄ እየገደለ እያሰረና እያሰቃየ ሥልጣኑን ለማቆየት በሚያደርገው ጥረት እስካሁን ከሆነው የወደፊቱ ሊከፋ እንደሚችል በጉልህ እየታየ ባለበት በዚህ ወቅት በተቃውሞው ጎራ ወቅቱን የሚመጥን -ራሱን በራሱ አደራጅቶ ነጻነት ወይንም ሞት ብሎ በጀመረው ትግል መስዋእትነት እየከፈለ ባለበት፣ስለ ነገ መታሰብ ስለ ነገም ተጨንቆ መስራትመነታረኩን ትተን ፤አደጋን በቀነሰ ሁኔታ ወያኔን ማስወገድእያደረሰ ያለውን አደጋ በመከላከልና ትግሉን በማጠናከር ለድል የሚበቃበትን ስራ ለመስራት ሁለትና ሶስት አይነት አማራ የለም የትም ይኑር አማራ ሁሉ አንድ ነው፣ አንድነት ሀይል ነው፣ ወያኔ የሚንበረከከውና ቅስሙ የሚሰበረውም አንድ ሁነን ሲያየን ነው፣ ሂዩመን ራይት አክቲቪስቶችና ሶሻል ሚዲያዎችም መፃፍና መናገር ካለባቸው አንድና አንድ ስለሆነው አማራ ብቻ ነው። እንደዚያ ሲሆን የኛ ጡንቻ ሲፈረጥም የወያኔ ይላላል፣ የኛ ምሽግ ሲገነባ የወያኔ የውሸት ካብ ይፈርሳል፣ መተባበሩ ግድ ነው።

ይህ ትግል የኢትዮጵያዊያን በሙሉ ትግል ነው። ይህ ትግል የዛሬ ነው።ይህ ትግል በሀገራዊ ራዕይና ተልዕኮ በመሳተፍ ከያንዳንዳችን የሚጠብቀው አስተዋፅዖ አለ። በርግጥ የሀገራችን የኢትዮጵያ ታጋዮች ያሉት በሀገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ዛሬ ከፍተኛውን መስዋዕትነት በመክፈል፤ከስህተት ወደ ጥፋት ከተሸጋገረው የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት /ከህወሃት ወያኔ ሰዎችና የኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር ሌት ተቀን በኑሯቸው እየተገደዱ፣ እየተሰቃዩ፣ በእስር ቤት እየተንገላቱ፣ እየተቀሙ፣ ግፍና የበደል በደል ለማስቆም በኢትዮጵያዊነት ትውፊት ለኢትዮጵያ ያሉት ታጋይ ልጆች ናቸው የሕዝብ ጠላቶች መወገድ መሠረታዊ ስለሆነ፤ መተባበሩ ግድ ነው።የኢትዮጵያ ጉዳይ፤ ከንብረት፣ ከኑሮ የበለጠ ክብር የምንሠጠው ሀቅ ነው

“እንተባበር"ሁሉም ዘብ ይቁም በቦታው”

ኢትዮጵያ በቆራጥ ልጆቿ ታፍራና ተከብራ ትኖራለች!

ሰልፍ የጀግና ድል የእግዚአብሄር ነው።

Gabriel Bezuneh